

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከኦገስት 1-10/2025 የነበረዉ የአየር ሁኔታ ግምግማ

# እንዲሁም

# ከኦገስት 11-20 እና ከኦገስት 21-31/2025

# የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦገስት 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ሰሜን ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ቦሌ 32.2፣ አርባምንጭ 40.3፣ በህር ዳር 42.3፣ 38.1፣ ኮምቦልቻ 66፣ ቢሾፍቱ 38፣ 31፡፡ ድሬዳዋ 40.4፣ ጎንደር 30.3፣ ጎሬ 39.7፣ ጅማ 55.2፣ መቀሌ 50.4፣ 51፣ መተሃራ 32.9፣ ነቀምት 167.6፣ 52.8፣ 33.4፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 46.5፣ አዴት 41.5፣ አዲግራት 40.5፣ አይደር 38.3፣ አይራ 37.6፣ ሃሮማያ 40.4፣ አልጌ 30፣ አማን 31.2፣ 65.8፣ አምቦ 35.9፣ አምደወርቅ 37.8፣ 39፣ 38.9፣ 32.5፣ አይከል 36.1፣ ባቲ 30፣ ቡሂ 38.2፣ ቡለን 30፣ 40.2፣ ቻግኒ 33.2፣ 50፣ ጨዋቃ 30፣ ደባርቅ 51.5፣ ደብረ ብርሃን 32.7፣ 37.5፣ 32.8፣ ደብረ ወርቅ 30.7፣ ፍቼ 44.9፣ 34.4፣ ጋምቤላ 40.3፣ 44.7፣ 39፣ ጊዳ አያና 40.9፣ ጉንዶ መስቀል 32.7፣ 45፣ 30.2፣ 36.6፣ 48.6፣ ካቺሴ 105.2፣ ላሊበላ 39.2፣ ሊሙገነት 44.7፣ ማይጨዉ 33.5. ማጀቴ 36.1፣ ማንኩሽ 49፣ 59፣ ማሻ 70.4፣ 30.4፣ መሃል ሜዳ 58.2፣ 54.6፣ መኢሶ 47.5፣ መተማ 31.9፣ አዳማ 43.6፣ 59.4፣ ነራ ኤራ 32.6፣ ሰኮሩ 38፣ ሻሁራ 44.8፣ 33.3፣ ሽሬ 35.5፣ ተርጫ 37.8፣ ወገል ጤና 33.5፣ ወረኢሉ 44.9፣ 32.1፣ 39.7፣ አዲስ አለም 31.5፣ 32.5፣ አዲስ ዘመን 34.3፣ 42.2፣ 40፣ አዲ አርቃይ 40፣ 31፣ 32.5፣ አሺ 32.6፣ 32.8፣ አሳሳ 46.5፣ አታንጎ 57፣ አዋሽ ሽለቆ 41.3፣ 46.3፣ 30.1፣ 32.3፣ ቢላምቢሎ 37.7፣ ጫጫ 32.6፣ 53.6፣ ጨፌ ዶንሳ 48.4፣ 50.3፣ 52፣ 30.3፣ ምንደር ሰባት 31.3፣ ደበሌ 33.1፣ ደብረ ሲና 39.1፣ 50.4፣ 74.4፣ 31.7፣ ደጋን 32፣ ደነባ 54.1፣ደንጎለታ 46.4፣ 46.4፣ ደራ 45፣ እብናት 30፣ 30.6፣ እርምጭ 46፣ ፈረስ ቤት 31.2፣ ጋሸና 55.4፣ 34.2፣ 51.1፣ 34.2፣ 34.8፣ ጊናገር 35.7፣ 38.9፣ ጊሽ ራቢል 34.4፣ ሃሪ 30.2፣ 40.5፣ ሂርና 50.2፣ 59.4፣ ሆርዶዮ 70.2፣ 32.1፣ 31፣ ጅሁር 37.5፣ ካራሚሌ 51.4፣ 30.8፣ 91.8፣ ቀርሳ 34.8፣ 75.1፣ ቁሉቢ 32.5፣ 37.6፣ 47.5፣34.5፣ ኩሚ 64.5፣ 110፣ ሊበን 47.4፣ መካነ ኢየሱስ 38.3፣ 41.8፣ መልካ ጀበዱ 38.8፣ 37.4፣ መንዲዳ 34.2፣ መርሳ 32.8፣ 54.2፣ ሞላሊ 34.3፣ 41.9፣ ሙጊ 57፣ ሙጃ 30.3፣ ሮቢት 33.1፣ 32.5፣ 39.5፣ ሰቆጣ 35.6፣ ተርኮዲ 33.2፣ 33.7፣ ያንፋ 35.3፣ ይችላ 49.8፣ ምንደር አስራ አንድ 60፣ 39.5፣ 36.5፣ የሪ 125፣ 30፣ ወልዲያ 32.1፣ ኢዳግ አርቢ 30.4፣ 40.2፣ 45.3፣ ጎቢይር 38.9፣ 30.5፣ 36.4፣ 43.5፣


43.5፣ 48.3፣ 40.2፣ አዋሽ ሰባት 32.2 እንዲሁም አንኮበር 40፣ 41፣ 31.1፣ 70 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ108 በሚደርሱ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 60.0-167.6 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ60 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል  ነቀምት፣ የሬ፣ ኪሚ፣ ካቺሴ፣ ካራሚሌ፣ ቀርሳ፣ ጨለንቆ፣ ደብረ ሲና፣ መሻ፣ ሆርዶዮ፣ አንኮበር፣ ኮምቦልቻ፣ አማን፣ መንደር አስራ አንድ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡





ምስል፡1 ከኦገስት 1-10 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና  ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ እና የጋቢ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች ላይ ከ61-340 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡ ፡ በተጨማሪም የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ የምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች፤ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎ፤ ማኦ ኮሞ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ፋንቲ፣ አዉሲ፣ እና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ጥቂት የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ እና የሊበን ዞኖች፣አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ ከ11-100 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-8 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፤ ምስራቅና ምዕራብ ሓረርጌ፣ ከአማራ ክልል ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ አዊ፣ ዋግ ህምራ፣ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኙዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ ምምራቅ፣ ደቡብ ምስራቅና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ኤረር እና ፋፈን ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋና ሐረሪ ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የሆነ የዝናብ





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

በሌላ በኩል ኤሊዳር፣ ሰመራ፣ አይሻ፣ አዋሽ አርባ፣ ገዋኔ፣ ድሬ ዳዋ፣ ጎዴ፣ ቀበሪ ዳሀር፣ መተሃራ፣ አቦቦ፣ ዳሊፋጊ፣ መተማ፣ ጋምቤላ፣ ፉኙዶ፣ ጨፋ፣ ኑራ ኤራ፣ ሸርቆሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ ባቲ፣ መኢሶ እና ቴፒ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 31 እስከ 45.8 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል፡፡

## 1.2 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የነበረው የተስፋፋ እርጥበት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ እንደ ስንዴ፣ ገብስ፣ አጃ እና ጤፍ ለመሳሰሉት የብርዕ ሰብሎች፣ የጥራጥሬና የቅባት እህሎች እና ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በምስራቅና በሰሜን ምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የመጠጥ ውሃ እና የግጦሽ ሳር አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡


በአንፃሩ በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከነበረው ከባድና ተከታታይነት ካለው እርጥበት ጋር ተያይዞ የጎርፍ፣ የመሬት መንሸራተትና በሰብሎች ላይ የውሃ መተኛትና መጥለቅለቅ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ በተለይም ባሳለፍናቸው አስር ቀናት በምሁር አክሊል ወረዳ መገራን ቀበሌ ላይ የተስተዋለ የጎርፍ እና የመሬት ናዳ በንብረትና በሰብል ላይ ጉዳት አድርሷል፣ በተጨማሪም በጋምቤላ ክልል በተከሰተው የጎርፍ አደጋ በተዘሩ ሰብሎችና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል። እንዲሁም በአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ኤፍራታና ግድም ወረዳ ከባድ ነፋስ ቀላቅሎ የጣለው ዝናብ ባስከተለው ጎርፍና በተከሰተው የመሬት መንሸራተት በሰዎች ጤንነት፣ ሕይወትና ንብረት ላይ ጉዳት እንደደረሰ ከተለያዩ የመስክ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው ኦገስት የመጀመርያ አስር ቀን በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ተከዜ፣ ባሮ አኮቦ፣ መረብ ጋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አይሻ፣ በላይኛው እና በጥቂት ታችኛው ዋቢ ሸበሌ እና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በላይኛው እና በመካከለኛው አባይ እና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው ተከዜ፣ አዋሽ እና ባሮ አኮቦ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለገፀ ምድር ውሃ ሀብት አዎንታዊ አስተዋፅዖ እንደነበረው የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ የመስኖም ሆነ የሀይል ማመንጫ ግድቦች የተሻለ የውኃ አቅም እንዲኖራቸው አድርጓል። ሆኖም እንደተከዜ እና ቆቃ በመሳሰሰሉ ግድቦች የገባው ከፍተኛ የውሀ መጠን በተለይም ለታችኛው የተፋሰሱ አካባቢዎች አስጊ ደረጃ ላይ የደረሰ እንደሆነ ታይቷል። እንዲሁም በነበረው ከፍተኛ የገጸ ምድር የውሀ ፍሰት በቢሾፍቱ፤ በሰበታ እና ጋምቤላ ከተማ ጎርፍ በንብረት እና በቤቶች ላይ ጎዳት አስከትሎ ነበር፡፡ የተቀሩት በአብዛኛው አጋዴን፣ ገናሌ ዳዋ፣ መካከለኛው ዋቢ ሸበሌ፣ ታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሆነው ቆይተዋል (ካርታ 5) ።




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኦገስት 1 እስከ 10/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ


## 2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በኦገስት ወር ውስጥ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ሙሉ በሙሉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ የኦገስት ወር ከተቀሩት የክረምት ወራት በተሻለ ሁኔታ ሁሉንም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን አካቶ በመጠንም ሆነ በሥርጭት ከፍተኛ ደረጃ የሚደርስበት ወር ነው። ስለሆነም የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን በምዕራብ አጋማሽ በአብዛኛው የሀገሪቱ ሥፍራዎች ላይ ከ200-400 ሚ.ሜ እና በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ ከ400 ሚ.ሜ በላይ ይደርሳል። በእነዚህ አካባቢዎች የዝናብ ቀናትም በዚያው መልክ የሚጨምር በመሆኑ ከ18-30 ለሚደርሱት ቀናት ዝናብ ይኖራል። በሌላ በኩል በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይም ቢሆን የዝናቡ መጠንና ሥርጭት እየተስፋፋ የሚሄድ በመሆኑ ከ6-20 ቀናት ያህል እስከ 300 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ በአማካይ ይኖራል።

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት ሁለተኛዉ አስር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ


በኦገስት ሁለተኛዉ አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው፣ ምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ይኖራቸዋል (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ የሰሜን ምስራቅ፣ ምስራቅ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ እና በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

በሚቀጥሉት አስር ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከመካከለኛ እስከ ከባድ (ከ11-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛው፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7)፡፡

**Exceptional Rainfall for 11-20 Aug 2025**




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን


ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ ምዕራብ አርሲ እና አርሲ፣ | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች | ከባድ መጠን (ከ30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ እና ባስኬቶ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በኦገስት ሁለተኛዉ አስር ቀናት ከሚኖረው የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በኤሊዳር፣ ዱብቲ፣ ሰመራ፣ ቡሬ፣ አሳይታ፣ ሁንዱፎ፣ ገዋኔ፣ ሚሌ፣ ዳሊፋጊ፣ አይሻ፣ ጉሊና፣ አዋሽ አርባ፣ ባቲ፣ ዶሎ አዶ፣ ዳዋ፣ ጎዴ፣ አቦቦ፣ ቋራ፣ አዋሽ ፈንታሌ፣ ጭፍራ፣ ላሬ፣ መተሃራ እና ፉኙዶ አከባበዎች ላይ ከ30 እስከ 38 ዲግሪ ሴልሺየስ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 8)፡፡




ካርታ 8 እ.ኤ.አ. ከኦገስት 11-20, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## 2.4 እ.ኤ.አ ከኦገስት 21 እስከ 31/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኦገስት የመጨረሻው አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በበለጠ ሁኔታ እየተጠናከሩ የሚሄዱበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በፀሀሓይ ሃይል ተግዘዉ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ በረዶ የቀላቀለ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡

በመጪዎቹ የኦገስት ሶስተኛው አሥራ አንድ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከዚሁ ጋር በተያዘም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

## 2.5 እ.አ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ በሰሜን ምስራቅ፣ በምስራቅ፣ በመካከለኛዉ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በደቡብ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት ይኖራል፡፡ በመሆኑም የሚኖረው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፤ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ እና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች የዋግ ህምራ፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ ትግራይ፣ የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፣ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የአፈር ውስጥ እርጥበት መሻሻል<br>• ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በቡቃያ ሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት<br>• ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የመሬት መንሸራተት<br>• የአረም መስፋፋት የአፈር ማዳበሪያና ፀረ ተባይ ኬሚካል መታጠብ | • በማሳዎች ውሰጥ የውሃ ማንጣፈፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት ያስፈልጋል<br>• የአፈር መሸርሸር ስጋትን ለመቀነስ የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• የማዳበሪያና የፀረ ተባይ ኬሚካል አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>• አረምን በወቅቱ ማረም |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምዕራብ አርሲ እና አርሲ፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ ሁሉም ሲዳማ የክልሉ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ የወላይታ፣ ጎፋ እና ባስኬቶ፣ የማሂ፣ ሀሪ፣ ቀልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት በቂ እርጥበት መኖር<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በቡቃያ ሰብሎች ላይ የውሃ መተኛት<br>• የአፈር መሸርሸር<br>• የአረም መስፋፋት<br>• የደረሱ የበልግ ሰብሎች ለመሰብሰብ አስቸጋሪ መሆን | • ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራት<br>• የአፈር መሸርሸር ስጋትን ለመቀነስ የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• የማዳበሪያና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር<br>• አረምን በወቅቱ ማረም፣<br>• የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በደረቅ ሰሞናተ መሰብሰብ |
| ምዕራብ ሐረርጌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • በጥቂት ቦታዎች ላይ የአፈር ዉስጥ እርጥበት ማነስ<br>• | • የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>• የዝናብ ውሀ ማሰባሰብና በደረቅ ሰሞናት መጠቀም<br>• ማሳን በየጊዜው መጎብኘትና የሰብል ጥበቃ ስራን ማከናወን<br>• ወሀን አክሞ ጥቅም ላይ ማዋል |
| **በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ጉጂ እና ቦረና ዞኖች፣ ጋሞ፣ ጌድዮ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች፣ የኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ቆራሂ እና ዳዋ፣ ዞኖችች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የደረሱ የበልግ ሰብሎችን ለመሰብሰብ | • ከፍተኛ ትነት መኖር<br>• | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>• የመኖ አቅርቦትን ማረጋገጥ |

## 2.6 እ.ኤ.አ ከኦገስት 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በቀጣይ ኦገስት ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው የክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ አልፎ አልፎ ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ፣ እንዲሁም የወንዞች ከፍታ መጨመር በተጨማሪም በላይኛው ተፋስስ በሚነሱ ወንዞች በታችኛው ተፋሰሶች ላይ የወንዞች መጥለቅለቅ የማስከተል እድል ይኖረዋል። በተለይም በአዋሽ ተፋሰስ አዋሽ ወንዝ ዳርቻ እና በኦሞ ጊቤ ተፋሰስ ኦሞ ወንዝ ዳርቻ እንዲሁም በአብዛኛው ክረምት ተጠቃሚ ተፋሰሶች በረባዳማ እና ረግረጋማ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች አካባቢ ከፍተኛ ሰጋት ሊኖር ይችላል። በመሆኑም ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ መረብ ጋሽ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ አይሻ፣ ላይኛው እና መካከለኛ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው ዋቢ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ | ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት | የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መጨመር<br>የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ መጠን መጨመር<br>የከርሰ ምድር የውኃ መጠን መሻሻል<br>የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን መጨመር | • የወንዞች መሙላት<br>• የቅፅበታዊ ጎርፍ ስጋት መጨመር<br>• በውሃ መያዣዎች ላይ የደለል ስጋት መጨመር<br>• የፍሳሽ መውረጃዎች በደለል እንዲሁም በጠጣር ቆሻሻ መዘጋት | • የጎርፍ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት<br>• የጎርፈ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት<br>• ፍሳሽ ሊዘጉ የሚችሉ ቆሻሻዎች በተገቢ ሁኔታ ማስወገድ<br>• ከፍተኛ ወራጅ ውሀን በእግርም ሆነ በቀላል ተሽከርካሪ ለማቋረጥ አለመሞከር<br>• የዝናብ ውሀ ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• የጎርፍ ተጽዕኖ ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየ ጊዜው መከታተል |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው መካከለኛው እና የታችኛው<br>• ገናሌ ዳዋ፣ ዋቤ ሸበሌና ኦጋዴን | ከመጠነኛ እስከ ደረቅ ሁኔታ | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት መቀነስ | • ዝቅተኛ የውሀ ፍሰት<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ አጥረት<br>• ከፍተኛ ትነት | • የሚገኘው መጠነኛ የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል በተግቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም<br>የሚገኘውን መጠነኛ የዝናብ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል |

Ethiopian Meteorology Institute